በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት

ባህል፣ ቱሪዝምና ፓርኮች ልማት ቢሮ

የባጉሳ ተፈጥሮ ደንን ህጋዊ እውቅና ለማሰጠት የተዘጋጀ

ደጋፊ ሰነድ

ሚያዚያ 2003 ዓ.ም

ማውጫ

1. መግቢያ 1

2.ዓላማ.....2

2.1 አጠቃላይ ዓላማ 2

2.2 ዝርዝር ዓላማዎች.....2

3.የቦታው መገኛ፣ ስፋትና የአየር ንብረት 3

3.1 መገኛ 3

3.2 የአየር ንብረት.....3

4. በታሳቢ ጥብቅ ቦታው ውስጥ የብዝሀ-ህይወት ሀብቶች 3

4.1 እጽዋት 3

4.2 አዕዋፋት 4

4.3 የዱር እንስሳት 4

5. የባጉሳ ተፈጥሮ ደን ታሪክና ክለላ 4

6. የቦታው ጥብቅ ስፍራ የመሆን አቅም.....5

6.1 ጥብቅ ስፍራው የሚኖረው ጠቀሜታ 5

6.2 ጥብቅ ቦታ የመሆን ማረጋገጫ መስፈርቶች 6

7.በታሳቢ ብሄራዊ ፓርኩ ላይ ያሉ ተጽዕኖዎች 8

8.በባኩሳ ታሳቢ ብሄራዊ ፓርክ አካባቢ የሚኖረው ህብረተሰብ አኗኗር

ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ሁኔታዎች 9

9. ማጠቃለያ 14

መግቢያ

በአገራችን የሚገኙ ብዝሃ ሕይወት ሀብቶች ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተመናመኑና ቁጥራቸው እየቀነሰ በመምጣቱ ትኩረት ሰጥቶ መጠበቅና አገራዊና አካባቢያዊ ጠቀሜታቸውን ማጉላት አስፈላጊ ነው፡፡ በኢትዮጵያ የዱር እንስሳት አጠቃቀም የረጅም ጊዜ ታሪክ ያለውና ዘመናትን ያስቆጠረ ቢሆንም የዱር እንስሳትን መጠበቅ የተጀመረው በ1901 ዓ/ም በዳግማዊ ሚኒሊክ ዘመነ መንግስት እንደሆነ ተረጋግጧል፡፡ በዚህም ወቅት ሕገ ወጥ አደን በተለይም የዝሆን አደን ክልክል መሆኑ ታውጇል፡፡ በኢትዮጵያ የዱር እንስሣት ጥበቃ ሁለተኛ አዋጅ በአጼ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት በ1923 ዓ/ም በእርሻ ሚኒስቴር ረቆ ሳይታወጅ ቀርቷል፡፡ በዚህም አዋጅ አደን ካለመንግሥት ፍቃድ እንዳይካሄድና በተወሰኑ አካባቢዎች ብቻ እንዲከናወን ተወስኖ ነበር፡፡ ከዚህም በኋላ የዱር እንስሳት ጥበቃና ልማት አዋጅ በ1936 ዓ/ም በመንግሥት የወጣ ሲሆን በ1938 ዓ/ም የአዋጅ ማስፈፀሚያ ደንብ በእርሻ ሚኒስቴር ወጥቶ በዚህ ደንብ ላይ በመመሥረት ሚኒስቴሩ የዱር እንስሳት አደን ፈቃድ ሲሰጥ ቆይቷል፡፡

በ1956 ዓ.ም በሃገሪቱ የዱር እንስሳት ክምችት ያላቸውን ቦታዎች የሚያጠና የዩኔስኮ ቡድን ወደ ኢትዮጵያ መጥቶ በዱር እንሰሳት ብዛት የሚታወቁትን የደቡብ ፣ የደቡብ ምዕራብ ፣ የሰሜንና የምሥራቅ የሀገሪቱን ክፍሎች በማጥናት አንዳንዱ ቦታዎች ከፍተኛ የዱር እንስሳት ሀብት እንዳላቸው የተረጋገጠበት ወቅት ነበር፡፡ በዚህ ጥናት የዱር እንስሳትን የሚያስተዳድር መ/ቤት እንዲቋቋም ሐሳብ ስለቀረበ የዱር እንስሳት ጥበቃና ልማት ድርጅት በ1957 ዓ.ም ተቋቋመ፡፡ ከዚህ በኋላ መ/ቤቱ በተለያዩ ጊዜያት ፓርኮችን ፣ መጠለያዎችን ፣ ጥብቅ ክልሎችንና የቁጥጥር አደን ቀበሌዎችን አቋቁሟል፡፡

በአማራ ብሔራዊ ክለላዊ መንግስት ቀደም ሲል ከ41 አመት በፊት ተቋቁሞ ሕጋዊ እውቅና ካገኘው የስሜን ተራሮች ብሔራዊ ፓርክ በጠጨማሪ የአላጥሽንና የቦረና ሳይንትን ብሄራዊ ፓርኮች አጥንቶ የብሄራዊ ፓርክ የጥብቅ ስፍራነት ደረጃ እንዲያገኙ አስችሏል፡፡

በአማራ ክልል ውስጥ በርካታ ብርቅየና አለማቀፋዊ ፣ አገራዊና አካባቢያዊ ጠቀሜታ ያላቸው ከ50 በላይ አጥቢ እንስሳት 450 በላይ የአእዋፍ ዝርያዎች እንዲሁም የተለያዩ የዕጽዋት ዝርያዎች ፤ ባሕላዊና ሃይማኖታዊ እሴቶች የመኖራቸውን ያሕል ተገቢውን ጥበቃና እንክብካቤ በማድረግ ከዘርፉ መገኘት የነበረበት ጥቅም አልተገኘም፡፡ በክልሉ በርካታ የዱር እንስሳት መኖራቸው ብቻ ሳይሆን ማራኪ የሆነው አካባቢያቸውና አለማቀፋዊ እውቅናና አድናቆት የተቸራቸው የተፈጥሮ ገጽታዎች ፣ ተራሮች ወንዞችና ሸንተረሮች እየተደረገላቸው ያለው ጥበቃ አነስተኛ በመሆኑ ካሁን በፊት የጥበቃ ደረጃ ካገኙት 3 ብሄራዊ ፓርኮች በተጨማሪ የመንዝ የማህበረሰብ ጥብቅ ስፍራ እና የባኩሳ ጣሳቢ ጥብቅ ስፍራዎች ተጠንተው ህጋዊ የጥበቃ ደረጃ እንዲሰጣቸው በመጠባበቅ ላይ ናቸው፡፡

የባኩሳ ታሳቢ ብሄራዊ ፓርክ በአማራ ብሄራዊ ክልል በአዊ ብሄረሰብ ዞን በጃዊ ወረዳ ውስጥ የሚገኝ ሲሆን ታሰቢ ብሄራዊ ፓርኩ ከእጂባራ ከተማ 210 ኪ.ሜ አነንዲሁም ከወረዳው ዋና ከተማ ከሆነችው የፈንድቃ ከተማ 60 ኪ.ሜ ይርቃል፡፡ የክልሉ ባህል፣ ቱሪዝምና ፓርኮች ልማት ቢሮ የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት አስፈጻሚ አካላትን ለማራጀት በወጣው አዋጅ ቁጥር 176/2003 ከተሰጡት ሥልጣንና ኃላፊነቶች አንዱ በከፍተኛ ደረጃ እየተጐዳ ያለውን የዱር እንስሳትና የመኖሪያ አካባቢያቸውን በመጠበቅና በማልማት ለአካባቢው ህዝብና ለአገሪቱ እድገት ተገቢውን ፣ ኢኮሎጅካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጠቀሜታ እንዲሰጥ ለማድረግ በክልሉ ውስጥ ጥብቅ ሥፍራ የመሆን አቅም ያላቸውን ቦታዎችና ብዝሀ-ህይወት ሃብቶችን ጥናት በማካሄድ ፣በመከለልን ህጋዊ ዕውቅና ማሰጠት ነው፡፡ በዚህም መሰረት የሳህል በርሃ እንዳይስፋፋ የአረንጓዴ ዘብ በመሆን የሚያገለግለውን የባኩሳን የተፈጥሮ ደን ማልማትና መጠበቅ በዚች ምድር ላይ ለመጥፋት የተቃረቡትን የሶረኔ ቆቅና ተኩላ ለመጠበቅ ከማስቻሉም በላይ ሽመልንና የእጣን ዛፍን የዘቦታ ጥበቃ /In-situ conservation/ ለማድረግ የሚያስችል ቦታ ነው፡፡

በባኩሳ ደን ውሰጥ ተጠልለው የሚኖሩ የዱር እንስሳት በአደንና በሰደድ እሳት ምክንያት ቁጥራቸው ቢቀንስም በጥናት መኖራቸው የተረጋገጠ ከአጥቢ የዱር እንስሳት መካከል የቆላ አጋዘን፣ ድኩላ፣ ከርከሮ፣ ዝንጆሮ ፣ ፌቆ፣ ነብር ፣ ጉሬዛ፣ ቀይ ጦጣ፣ አሳማ የመሳሰሉት በታሳቢ ብሄራዊ ፓርኩ እንደሚኖሩ የተረጋገጠ ሲሆን አንበሳና ተኩላ በተወሰነ ወቅት ከአጎራባች ቤንሻንጉል ጉምዝ ክልል ከባግልቲ በመነሳት አካባቢውን በመጠቀም የሚመለሱ መሆኑን ማረጋገጥ የተቻለ ሲሆን ቀደም ሲል የነበሩ አሁን የጠፉ /የተሰደዱ/ እንደ ውደንቢ፣ ጨሌ ባለጋሜ /Roan antelope/ና ቶራ ቆርኬ፣ (Tora hartebeest) የቦታው የቅርብ ጊዜ ታሪክ ናቸው፡፡

ታሳቢ ብሄራዊ ፓርኩ የSudano-guinea ባዮምን የሚወክል ሲሆን ይህን አካባቢ በማልማትና በመጠበቅ በቆላማው አካባቢ የሚኖሩ የዱር እንስሳትንና እጽዋትን ለመጠበቅ፣ ህገወጥ የዱር እንስሳት አደንን ለመቆጣጠር ፣የሰደድ እሳትን ለመቆጣጠርና በአካባቢው ያለውን ህገወጥ የእርሻ መስፋፋት ለመቆጣጠር የሚያስችል በመሆኑ ይህ ደጋፊ ሰነድ ተዘጋጂቷል፡፡

ዓላማ

2.1.አጠቃላይ ዓላማ

በባኩሳ ታሳቢ ብሄራዊ ፓርክ እስከአሁን የተጠኑ ዝርዝር ጥናቶችን መነሻ በማድረግና ዳር ድንበሩን ከተጠቃሚው ህብረተሰብ ጋር በተደረገው ክለላ መሰረት በታሳቢ ብሄራዊ ፓርኩ ውስጥ ያለውን ሃብት መጠበቅ እንዲቻል ቦታው የብሄራዊ ፓርክነት ደረጃ የሚያገኝበትን ህጋዊ እውቅና ለማሰጠት አስፈላጊ የሆኑ መሰረታዊ መረጃዎችን መሰብሰብ መተንተንና ማደራጀት፡፡

2.2.ዝርዝር ዓላማዎች

- የቦታውን ዋና ዋና የዱር እንስሳትና ዕጽዋት ሃብት ፣የመሬት አቀማመጥ ፣የአየር ንብረት መረጃ አጠቃሎ ለማቅረብ ፣

- ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ኢኮሎጂያዊ ሁኔታዎች ጥናቶችን መነሻ በማድረግ ለማደራጀት፣
- የአካባቢውን ህብረተሰብና ውሳኔ ሰጭ አካላት በማስተባበር የድንበር ክለላውን ካርታ አዘጋጂቶ በማቅረብ የአካባቢው ህብረተሰብ እንዲስማማበት ማድረግ፣
- ታሳቢ ጥብቅ ቦታው የብሄራዊ ፓርክነት ደረጃ የሚያገኝበትን ህጋዊ እውቅና ለማሰጠት

3.የቦታው መገኛ፣ ስፋትና የአየር ንብረት

3.1 መገኛ

የባጉሳ የተፈጥሮ ደን በአብክመ በአዊ ብሔረሰብ ዞን በጃዊ ወረዳ ውስጥ የሚገኝ ሲሆን በምዕራብ የቤንሻንጉል ጉምዝ ክልል በምስራቅ የባጉሳ ማሪያም ቀበሌ በሰሜን የባጉሳ ኪዳነምህረት ቀበሌ በደቡብ የባጉሳ ማሪያም ቀበሌና የቤንሻንጉል ጉምዝ ክልል ያዋስኑታል፡፡

በዚህ ጥናትና ክለላ ከባጉሣ ማሪያም ቀበሌ 41311.35 ሄክታር፣ከባጉሣ ኪዳነምህረት ቀበሌ 3416 ሄ/ር በአጠቃላይ የታሣቢ ጥብቅ ቦታው የቆዳ ስፋት 44727.35 ሄ/ር ተያያዥነት ያለው የተፈጥሮ ደን ሲሆን ማራኪ ገጽታ ያላቸውን ሰንሰለታማ ተራራዎች፣ በርካታ ወንዞችና ሜዳማ መሬቶችን የያዘ ነው፡፡ መልክዓ-ምድራዊ አቀማመጡም ከ$36^0 0^1 3.2"$ እስከ $36^0 19^1 7.4"$ ምስራቅ ሎንግቲዩድ ከ$11^0 39^1 30.7"$ እስከ $11^0 59^1 27.1"$ ሰሜን ላቲትዩድ፣ መካከል ይገኛል፡፡

3.2. የአየር ንብረት

የባጉሳ ታሳቢ ብሄራዊ ፓርክ ከባህር ወለል በላይ ያለው ከፍታ ከ710 እስከ 1200 ሜትር ሲሆን ታሳቢ ብሄራዊ ፓርኩ 100% የቆላ አየር ቀጠና ውስጥ ይገኛል ፡፡ የባጉሳን የተፈጥሮ ደን የሙቀት መጠን ስንመለከት ለቦታው የተመዘገበ የሜትሮሎጅ መረጃ ባይኖርም በጃዊ ወረዳ ወስጥ በታሳቢ ጥብቅ ቦታው ቅርብ ርቀት ላይ (ሞሰቢት አካባቢ) የተፈጥሮ ደኑን ይዘትና ሥርጭት በተመለከተ ለዶክትሬት ዲግሪ መመረቂያ ጽሑፍ (Thesis) ከተካሄደ ጥናት ላይ የተወሰደው መረጃ እንደሚያመለክተው የቦታው ወርሄዊ ዝቅተኛና ከፍተኛ የሙቀት መጠን ከ15.7 እስከ 31.5 ዲግሪ ሴንቲ ግሬድ ሲሆን አማካዩ ደግሞ 23.6 ዲግሪ ሴንቲ ግሬድ ነው፡፡ ዓመታዊ አማካይ የዝናብ መጠኑም 1283 ሚ.ሜ እንደሆነ መረጃው ያመለክታል፡፡

4. በታሳቢ ጥብቅ ቦታው ውስጥ የብዝሀ-ህይወት ሀብቶች

4.1 እጽዋት

የባጉሳ የተፈጥሮ ደን አካባቢ ሰፊ የሆነ የቆዳ ስፋትና በወሳይ የእፅዋት ሽፋን ፣ የቆላውን /Combretum-terminalia woodland ecosystem/ ሥርዓተ ምህዳር የሚወክል ሲሆን በጥናትና ክለላው ወቅት ከ58 በላይ የዛፍና ቁጥቋጦ ዝርያዎች ተለይተዋል ለአብነት ያህል በታሳቢ ጥብቅ ቦታው ውስጥ መኖራቸው የተረጋገጡ የተለያዩ የሣር፣ የዛፍና የቁጥቋጦ ዝርያዎች እንደ ኮመር፣ የጣን ዛፍ፣ ሽመል ፣ ዳርሌ፣ ዛና፣ የቆላ ዋንዛ፣ አባሎ፣ ዋርካ፣ ባምባ፣ ሾላ፣ ቁርቁራ፣ ጥቁር እንጨት፣ ዞቢ፣ ጋምቢሎ፣ እሸ፣ ጋቫ፣ አደር ፣ ግማርዳ፣ ወንበላ ፣ ክራክራ፣ ጫሪያ የመሳሰሉት በብዛት ይገኛሉ፡፡ ከእነዚህ ውስጥ እንደልብ የማይገኙና ለመጥፋት

የተቃረቡ /በመጥፋት ላይ ያሉ/ መጠበቅ የሚገባቸው እንደ ሽመል፣ ጥቁር እንጨት፣ የቆላ ዋንዛ፣ ኮመር ፣ የጣን ዛፍ፣ ዶቅማ፣ ላሎ፣ ዋርካና ሾላ የመሳሰሉ ዛፎች ይገኙበታል፡፡

የደኑ ሽፋን አሁንም ቢሆን ከ80% በላይ የተፈጥሮ ገፅታውን እንደጠበቀ የሚገኝ ነው፡፡ ስለሆነም ቦታው ከተጠበቀና የነዋሪውም ግንዛቤ ከዳበረ በአጭር ጊዜ ውስጥ የተፈጥሮ ሃብቱ ወደ ነበረበት ሁኔታ ሊመለስ ይችላል፡፡

4.2 አዕዋፋት

አዕዋፍን በተመለከተ በባኩሳ ታሳቢ ብሄራዊ ፓርክ ውስጥ የሚገኝ የአእዋፍ ብዛት መረጃ በትክክል ልተጠና ቢሆንም ታሳቢጥብቅ ስፍራው በተጠናበት ወቅት ከ31 በላይ የአዕዋፍ ዝርያዎች አንደተጠለሉበት የተመዘገበ ሲሆን ከነዚህም ውስጥ ለመጥፋት የተቃረበችውን የሶረኔ ቆቅና ኔሎችም Glossy Ibis,Helmeted guineafwol,Hooded Vulture,Greater Honeyguide,White-backed Vulture,Woolly-necked stork and Abyssinian Ground Hornbill የመሳሰሉት የአዕዋፍት ዝርያዎች ይገኙበታል፡፡

4.3 የዱር እንስሳት

በህዝብ ቁጥር መጨመር ምክንያት በብዝሃ-ህይወት ሃብቶች ላይ ጉዳት እየደረሰ ቢሆንም በተለይም የዱር እንስሳቱ ቁጥር ገደብ የለሽ በሆነ አደን ቢመናመንም በተከታታይ ዓመት በእሳት ቃጠሎ ተተኪ እፅዋት ስለተገዱና ከፍተኛ የሆነ የዱር እንስሳት አደን ስለተካሄደ የዱር እንስሳቱን ቁጥር ቢቀንሰውም በጥናቱ ወቅቱ መኖራቸው የተረጋገጠ ከ28 በላይ ታላላቅ አጥቢ የዱር እንስሳት መካከል የቆላ አጋዘን፣ ድኩላ፣ ከርከሮ፣ ዝንጀሮ ፣ ፌቆ፣ ነብር ፣ ጉሬዛ፣ ቀይ ጦጣ፣ አንበሳ፣ ተኩላ፣ አሳማ፣ ሚዳቋ፣ ጅብ ፣ ጀርባው ጥቁር ቀበሮ፣ ጃርት፣ ጥሪኝ የመሳሰሉት ሲገኙ ቀደም ሲል የነበሩ አሁን የጠፉ ፣ /የተሰደዱ/ ውድንቢ፣ደፋርሳ ፣ ጨሌ ባለጋሜ /Roan antelope/ና ቶራ ቆርኬ፣ (Tora hartebeest) አብዛኛዎቹ ነዋሪዎች የሚያውቁት የቦታው የቅርብ ጊዜ ታሪክ ናቸው፡፡ ከተራማጅና ተሳቢዎች ደግሞ እንደ ዘንዶ ፣ አዞ፣ አርጃኖና የተለያዩ እንሽላሊትና የእባብ ዝርያዎች ይገኛሉ፡፡

5. የባኩሳ ተፈጥሮ ደን ታሪክና ክለላ

የጃዊ ወረዳ 515400 ሄ/ር የቆዳ ስፋት ሲኖረው ከዚህ ውስጥ የባኩሳ ታሳቢ ብሄራዊ ፓርክ ከ44727 ሄ/ር ወይም የወረዳውን 8.7% ይሸፍናል፡፡ ስያሜውን ያገኘው በአካባቢው የባኩሲ ባላባቶች ይኖሩ እንደነበርና ስሜውንም ከዚሁ እንዳገኘ የአካባቢ ነዋሪዎች ይናገራሉ፡፡ የባኩሳ የተፈጥሮ ደን የCombretum terminalia woodland ecosystemን ስርዓተ-ምህዳር የሚወክል ሲሆን ተፈጥሯዊ ይዘቱ ብዙም ሳይቀየር ከቆዩ ለረጂም አመታት ከቆዩት የሃገሪቱ ክፍሎች አንዱ ነው፡፡ ደኑ በክልሉ ውስጥ ትኩረት ከተሰጣቸው የተፈጥሮ ደን ዝርዝር ውስጥ ባይገኝም የአዊ ብሄረሰብ ምክር ቤት የአካባቢውን ጥብቅ ስፍራ የመሆን አቅም በመገንዘብ በ2000ዓ.ም ብሄራዊ ፓርክ እንዲሆንና ዝርዝር ጥናቱ በፓርኮች ልማትና ጥበቃ ባለስልጣን እንዲታይ እንዲሁም የጥበቃ ስራውን የወረዳው ግብርና ጽ/ቤት ዘበኛ በመቅጠር እንዲያስጠብቅ የተወሰነ ሲሆን10

ዘበኛዎችን በመቅጠር በማስጠበቅ ላይ ይገኛል፡፡ የብሄረሰብ ምክር ቤቱን ውሳኔ መነሻ በማድረግ የፓርኮች ልማትና ጥበቃ ባለስልጣን ባለሙያዎችን ወደ አካባቢው በመላክ የታሳቢ ብሄራዊ ፓርኩን ጥብቅ ስፍራ የመሆን አቅም ያረጋገጠ ሲሆን በጥናት ወቅቱ በውስጥ ይኖሩ የነበሩት አርሶ አደሮችን ማሰወጣት ካልተቻለ ብሄራዊ ፓርክ አድርጎ መከለሉ አስቸጋሪ መሆኑን ለብሄረሰብ ምክርቤቱ ባቀረበው ሪፖርት መሰረት 141 አባወራዎችን በማስወጣት ላይ ሲሆኑ ቦታው የብሄራዊ ፓርክነት ደረጃ እንዲያገኝ ስራዎች በመሰራት ላይ ይገኛሉ፡፡ የአካባቢው ነዋሪ ህብረተሰብ ለአመታት ደኑን ሳይጨፈጭፍ ተጣጥመው እንደሚኖሩ ጥናትና ክለላ ባካሄድንበት ወቅት በዘላቂነት ሲጠቀምበትና ሲጠበቅ የቆየ መሆኑን ማረጋገጥ የተቻለ ሲሆን አሁን በአካባቢው ያለው የሰሊጥ ገበያ በተፈጥሮ ሃብቱ ላይ ጫና የፈጠረ ሲሆን የልማትና ጥበቃ ስራውን ወደተሻለ ደረጃ ለማሻሻል የብሄራዊ ፓርክነት ደረጃ እንዲያገኝ ስራዎች እየተከናወኑ ነው፡፡

6. ጥብቅ ስፍራ የመሆን አቅም

6.1 ጥብቅ ስፍራው የሚኖረው ጠቀሜታ

ሀ/ ሥነ-ምህዳራዊ ጠቀሜታ **/Ecological importance/**

- ሰዎች ከተፈጥሮ ጋር ያላቸዉ መስተጋብር ዘለቄታዊ የተፈጥሮ ገጽታ መኖርን ማረጋገጥ በሚያስችል መልኩ እንዲሆን ማድረግ ያስችላል፣
- በአካባቢው ያለው ስርዓተ ምህዳር እንዳይዛባ ከፍተኛ አስተዋፆ ያደርጋል ፣
- ለበርሀማነት ተጋላጭ የሆነው የዝቅተኛ ቦታዎችን ሰነምህዳር ለመጠበቅ ያስችላል፣
- በጥብቅ ስፍራው ውስጥ ያለው የብዝሃ ህይወት ሳይጠፋ እንዲኖር ያደርጋል፣
- በአካባቢው የሚገኙ የዱር እንስሳትና ዕፅዋት በአይነትም ሆነ በብዛት ይጠበቃሉ፣
- የተስተካከለ የውሃ ሃብት እንዲኖር ያስችላል (ከጥብቅ ስፍራው የሚነሱ ምንጮችና ጂረቶች አመቱን በሙሉ እንዲፈሱ ያስችላል)፡፡

ለ/ ኢኮኖሚያው ጠቀሜታ /Economic importance/

- በማህበረሰብ ጥብቅ ስፍራው ከጐብኝዎች ጋር ተያይዞ ከቱሪዝም አማራጭ ገቢዎች ለህብረተሰቡና ለመንግስት ገቢ ያስገኛል፣
- ከምርምርና ሣይንሳዊ ጥናት እንቅስቃሴ ጋር ተያይዞ የአካባቢውን ገቢና አቅም ያጐለብታል፣
- የኢኮ-ቱሪዝም እንቅስቃሴ ስለሚስፋፋ ለአካባቢው ህብረተሰብ አንድ የገቢ ምንጭ ይሆናል፡፡
- የአካባቢው የአየር ሚዛን ስለሚጠበቅ ከእርሻ ስራ የሚገኘው ገቢ ዘላቂና አስተማማኝ እንዲሆን ይረዳል፡፡

ሐ/ ማህበራዊ ጠቀሜታ /Cultural importance/

- ዓለማቀፋዊና ማህበረሰባዊ የሆኑ ጠቃሚ የባህልና ልምድ ልውውጥ ይኖራል፣

- በአካባቢው የሚገኙ ነዋሪዎች ደኑን ለመጠበቅም ሆነ በአገባቡ ለመጠቀም የሚያስችል ምቹ ሁኔታ ይፈጠራል፡፡

መ/ሳይንሳዊ ጠቀሜታ /Research uses/

- የዱር እንሰሳትና ዕፅዋትን ባሉበት ሁኔታና በተፈተሮአዊ አኗኗራቸዉ ለሚደረግ ምርምር በማእከልነት ያገለግላል ፣
- የባህላዊ መድሃኒቶችን ደህንነት በመጠበቅና በመንከባከብ ጥቅም ላይ በማዋል ሣይንሳዊ ጥናትንም ለማካሄድ ይረዳል፣
- በመጥፋት ላይ ላሉ የዱር እንስሳትና እጽዋት ላይ ለሚደረጉ ሳይንሳዊ ጥናቶችና ምርምሮች የተፈጥሮ ላቦራቶሪ በመሆን ሊያገለግል ይችላል፡፡

መ/ የተፈጥሯዊነት ጠቀሜታ /Naturalness/

- ተፈጥሯዊነትን ጠብቆ ለመቆየት ያስችላል፡፡ በዉስጡ ያሉትን ብዝሃ ህይወትና ሌሎች (አፈር፤ዉሃና የመሬት አቀማማጥ) በተፈጥሮአዊ ገጽታቸዉ ቆይተዉ ዘለቂታ ባለዉ መልክ ጥቅም እንዲሰጡና ተፈጥሮአዊ ይዘታቸዉ እንዳይጓደል ይረዳል፡፡

ሠ/ የቱሪዝም መስህብነት ጠቀሜታ /Importance of tourism attraction/

- አካባቢው የሰው ልጅን ቀልብ ሊስቡ የሚችሉ ማራኪ ገጽታወች የያዘ ከመሆኑም በተጨማሪ ተፈጥሯዊና ባህላዊ ቅርሶች በቅርብ እርቀት የትስኪ ፏፏቴ፣የዶንዶር ፏፏቴ ፣የገርቾ ፏፏቴ፣ የዘንገና ሃይቅ፣የትርባ ሃይቅ የሚገኙ ስለሆነ የመስህብነት ጠቀሜታውን የጎላ ያደርገዋል፡፡ ቦታው ህጋዊ እውቅና አግኝቶ ከተጠበቀ ዘላቂ ለሆነ ጥቅም ኢኮሎጅካዊ ፣ ኢኮኖሚያዊና የቱሪዝም መስህብ ማዕከል ሊሆን የሚችል

6.2 ጥብቅ ቦታ የመሆን ማረጋገጫ መስፈርቶች

በዓለማቀፍ የተፈጥሮ ሃብት ጥበቃ ህብረት IUCN መስፈርቶች መሠረት ብሔራዊ ፓርክ ሊያሰኙ የሚችሉ መመዘኛዎች መሠረት የባጉሳን የተፈጥሮ ደን በሚከተለው ሁኔታ መግለጽ ይቻላል፡፡

ሀ/ ወካይነት /representativeness/

- የባኩሳ ታሳቢ ጥብቅ ስፍራ ቦ የsudano-guinea biomeን የሚወክል ስለሆነ በጥብቅ ስፍራነት ቢከለል በልማት ቀጠናው ወካይ የሆነ የጥበቃ ቦታ ሊሆን ይችላል፡፡
- ከስርዓተምህዳር ውክልና በተጨማሪ የሽመልና የእጣን ዛፍን የዘቦታ ጥበቃ ለማድረግ ወካይ አካባቢ ነው፡፡

ለ/ የብዛ-ህይወት ክምችት / Diversity/

የአካባቢውን የብዝሃ-ህይወት ሃብት ስንመለከት ከ28 በላይ ታላለቅ አጥቢ የዱር እንእሳት ፣ ከ63 በላይ የዕፅዋት ዝርያዎች ፣ከ31 በላይ የአዕዋፍት ዝርያዎች መገኛ ሲሆን በተለይም ከዚህ ምድር ለመጥፋት የተቃረቡትን የሶረኔ ቆቅና ተኩላ ለመጠበቅ ወሳኝ ቦታ ነው፡፡

ሐ/ ልዩ መገለጫ / Distinctiveness/

- በአንጻራዊነት ሰፊ የሆነ የተፈጥሮ ደን ያለው በመሆኑና ሽመልን ለመጠበቅ የሚያስችል ቦታ ከመሆኑም በተጨማሪ ወቅታዊም ቢሆን ከክልሉ ካሉ ጥብቅ ስፍራዎች በተለየ ተኮላን ለመጠበቅ ያስችላል፡፡

መ/ የቦታ ስፋት /Area/ :- ታሳቢ ጥብቅ ቦታው ተያያዥነት ባለው መልኩ የባጉሳ ማሪያምና ባጉሳ ኪዳነ ምህረት ቀበሌዎችን ባካተተ ሁኔታ ክለላው የተካሄደ ስለሆነ የቦታው ስፋት 44727.35 ሄክታር በመሆኑና የ IUCN መስፈርት ከሚጠይቀው ዝቅተኛ ስፋት /1000ሄ/ር/ በላይ በመሆኑና ከዚህም አልፎ ቦታው ክልል ተሻጋሪ ጥብቅ ቦታ ማቋቋም የሚያስችልና ከቤንሻንጉል ጉምዝ ተመሳሳይ የተፈጥሮ ደን ሽፋንና ለዱር እንስሳት ዝውውር ምቹ ኮሪደር ያለው በመሆኑ፡፡

ሠ/ ቅርፅ /መጠነ ዙሪያ/shape/ ጥብቅ ስፍራዎች በሚቋቋሙበት ወቅት የጥበቃ ስራውን በቀላሉ ለማከናወንና በብዝሃ ህይወት ሃብቱ ላይ ሊደርስ የሚችለው ጫና እንዲቀንስ በተቻለ መጠን ዝቅተኛ መጠነ ዙሪያ እንዲኖራቸው ይጠበቃል ፡፡ በመሆኑም የባጉሳ ተፈጥሮ ደን መጠነ ዙሪያ በአንጻራዊነት ከጥብቅ ስፍራው ስፋት አንጻር ለጥበቃ ስራው አስቸጋሪ እንዳይሆን ተመጣጣኝ የሆነ መጠነ ዙሪያ አለው ፡፡

ረ/ ተፈጥሮአዊነት / Naturalness/ :- የህገ ወጥ ሰፋሪዎች የእርሻ እንቅስቃሴና እንዲሁም የነባር ነዋሪዎች መሬት ሽሚያና በደኑ ውስጥ ቤት ሥራ ካስከተለው የደን ምንጠራና ህገ-ወጥ የዱር እንስሳት አደን አሉታዊ ተፅዕኖ በስተቀር ቦታው የተፈጥሮ ገጽታውን እንደጠበቀ ያለ አካባቢ ነው፡፡

ሰ/ እንደልብ የማይገኙና መጠበቅ የሚገባቸው የዱር ህይወት፡- በአገሪቱና በክልሉ ውስጥ እንደልብ የማይገኙና ለመጥፋት የተቃረቡ መጠበቅ የሚገባቸው እንደ ሽመል፣ ጥቁር እንጨት፣ የቆላ ዋንዛ፣ ኮመር ፣ የጣን ዛፍ፣ ዶቅማ፣ ላሎ፣ ዋርካና ሾላ ዛፎች በዚህ ቦታ ሊጠበቁ የሚችሉ ሲሆን በዱር እንስሳት ደግሞ በመጥፋት ላይ ያሉ አንበሳ፣ ተኩላና እንዲሁም ብርቅዬ የሆነችውን ሶረኔ ቆቅ ጨምሮ ለወደፊት በበቂ ቁጥራቸው ተራብተውና ተጠብቀው ለቀጣዩ ትውልድ ለማስተላለፍ የሚቻልበት ቦታ ነው፡፡

ሸ/ ሥነ-ምህዳራዊ ጠቀሜታ/Ecological importance/

- ሰዎች ከተፈጥሮ ጋር ያላቸዉ በስተጋብር ዘለቄታዊ የተፈጥሮ ገጽታ መኖርን ማረጋገጥ በሚያስችል መልኩ እንዲሆን ማድረግ ያስችላል፡፡ በዚህም ዘለቄታዊ ጥቅም አለዉ፣
- በአካባቢው ያለው ስርዓተ ምህዳር እንዳይዛባ ከፍተኛ አስተዋፆ ያደርጋል ፣
- ለበረሀማነት ተጋላጭ የሆነው የዝቅተኛ ቦታዎች ሰነምህዳር ለመጠበቅ ያስችላል፣
- በታሳቢ ጥብቅ ስፍራው ውስጥ ያለው ብዝሃ ህይወት ሳይጠፋ እንዲኖር ያስችላል፣
- በአካባቢው የሚገኙ የዱር እንስሳትና ዕፅዋት በአይነትም ሆነ በብዛት ይጠበቃሉ፣
- የዱር እንስሳትና ዕፅዋት በቦታቸው እንዲጠበቁና እንዳይጠፉ ይረዳል፣
- የተስተካከለ የውሃ ሃብት እንዲኖር ያስችላል (ከታሳቢ ጥብቅ ስፍራው የሚነሱ ምንጮችና ጂረቶች አመቱን በሙሉ እንዲፈሱ ያስችላል)፡፡

ቀ/ በአካባቢው ላይ ያለ ጫና መጠን /Degree of interference/

- በደኑ ውስጥ የሰደድ እሳት በየአመቱ መካሄድ፣
- የደን ጭፍጨፋ በሰፊው ለሰሊጥ ምርት ሲባል መካሄድ፣

- የልቅ ግጦሽ መኖር፣
- ከ126 በላይ ነዋሪዎች በክልሉ ውስጥ መኖር፣
- ከሌላ አካባቢ እየመጡ ከአካባቢው ነዋሪዎች ጋር ግንኙነት በመፍጠር ህገ-ወጥ እርሻ ማካሄድ፣
- ህገ-ወጥ የዱር እንስሳት አደን ማካሄድ ዋነኞች ናቸው፡፡

በ/ የአካባቢው ሳይንሳዊ ጠቀሜታ /Scientific and monitoring uses/

- የዕጽዋትንና የዱር እንሰሳትን የተፈጥሮ አካባቢቸዉን ለማጥናት በሞዴልነት ያገለግላል ፣
- ለአካባቢ ክትትል በሚኖረው ጠቀሜታ የተፈጥሮ ሚዛን ለዉጥን መለካት ያስችላል፣
- የዱር እዕዋት ናሙናና ተፈጥሮአዊ እድገትንና በሰዎች ጣልቃ ገብነት የሚመጣዉን ለዉጥ ለመለየት ይረዳል

ተ/ በውስጡ የሚገኙ ብርቅየና ድንቅየ ዝርያዎች /Endemicity/

ከታለላቅ አጥቢዎች መካከል በአደጋ መዝገብ ውስጥ የተመዘገቡ አንበሳና ተኩላ በታሳቢ ጥብቅ ስፍራው *Panthera leo and Lycaon pictus ይገኙበታል*:: ከአዕዋፍ ዝርያዎች ውስጥ ደግሞ ብርቅዬዋ የሶረኔ ቆቅ *Francolinus hardwoodi* በዚሁ ቦታ ትገኛለች፡፡

ሰለሆነም **ከሀ-ተ** የተዘረዘሩትን መስፈርቶች ስንመለከት ጥብቅ ቦታ ለመሆን የሚያስችለውን መስፈርት የሚያሟላ ሲሆን ቦታው የብሄራዊ ፓርክነት ደረጃን ሊያገኝ የሚያስችለውን መስፈርት ስለአሟላ የጥበቃ ደረጃው ቢሰጠው ለጥበቃውና ዘላቂነቱ አስተማማኝ ይሆናል፡፡

7. በታሳቢ ብሄራዊ ፓርኩ ላይ ያሉ ተጽዕኖዎች

የአካባቢው ህብረተሰብ ሰፋሪውን ጨምሮ ስለተፈጥሮ ሃብቶች አያያዝና ዘላቂነት ያለው አጠቃቀም ግንዛቤ አናሳ መሆን፣

- ⇨ በታሳቢ ፓርኩ ውስጥ ከ126 አባውራዎች ያላነሱ መንደሮች (Settlement) መኖርና በድንበሩም ጭምር ብዙ መንደሮች መኖርና ለጥበቃው ስጋት መሆናቸው፣
- ⇨ ከተፈቀደ የኢንቨስትመንት ሥራ ውጭ ልዩ ጥቅም ለማግኘት በመሬት ባለሃብትነት ብቻ ለመጠቀም ጥረት ማድረግ፣ማለትም ታሳቢ ጥብቅ ቦታው ውስጥ ነባር የአገው ብሔረሰብ መንደር መኖርና ለመሬት ሽሚያ እየተባለ ወደ ቆላማው ክፍል እየወረዱ ቤት መሥራትና ህገ-ወጥ ሠፋሪዎችም ከቁጥጥር ውጭ በሆነ መልኩና ጡት በመጣባት ማስገባት፣
- ⇨ ህገ-ወጥ የዱር እንስሳት አደንና እንዲሁም ሽመል፣ ትላልቅ ዛፎችና የጣን ዛፍን ጨምሮ ከፍተኛ የሆነ የደን ጭፍጨፋ ማካሄድ፣
- ⇨ ተገቢው ቁጥጥርና ክትትል የማይደረግበት የኢንቨስትመንት የእርሻ ሥራ እንቅስቃሴ፣
- ⇨ የወንዝ አሳን በማላታይን መመረዝ፣

⇨ ወቅታዊ ክትትል በማድረግ ህገ-ወጥ ሰፋሪዎችንና አዳኞችን ለህግ አለማቅረብና ተገቢውን የእርምት እርምጃ አለመውሰድ ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

8. በባኩሳ ታሳቢ ብሄራዊ ፓርክ አካባቢ የሚኖረው ህብረተሰብ አኗኗር ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ሁኔታዎች

በአካባቢው በዋናነት የሚኖሬት የአገው ብሄረሰብ አባላት ሲሆኑ የአማራ ብሄረሰብ አባላትም በአካባቢው በሰፈራና በህገወጥ ሰፍረው ይኖራሉ፡፡ የታሳቢ ብሄራዊ ፓርኩ ከሁለት ቀበሌዎች ማለትም ከባኩሳ ማሪያምና ባኩሳ ኪዳነምህረት ቀበሌዎች የሚዋሰን ሲሆን የነዚህ ቀበሌዎች የኑሮ መሰረት የሆነው የእርሻ ስራ ሲሆን ይህም የሚከናወነው በመቆፈር፣በበሬና በአህያ በማረስ ነው፡፡ በዚህ የአስተራረስ ስርዓት በቆሎ፣ ማሽላ፣ ጤፍ፣ ዳጉሳ፣ ሽምብራ፣ ሩዝ፣ ኑግ፣ ለውዝ፣ የፈረንጅ ሱፍ፣ አኩሪ አተር፣ ሰሊጥ ያመርታሉ ፡፡ ከምግብ እህል ምርት በተጨማሪ ለገበያ የሚመረቱ እህሎች ከጊዜ ወደጊዜ እየጨመረ መጥቷል፡፡ በተለይ የሰሊጥ ገበያ መናር ለህገ-ወጥ ሠፈራና የተፈጥሮ ደን ጭፍጨፋ ከፍተኛ አስተዋፅኦ አድርጓል፡፡ ለአብነት ያህል በባኩሳ ማሪያም ቀበሌ የችክሪ በተባለችው ጦጥ ከ200 በላይ ህገ-ወጥ ሰፋሪዎች አሉ፡፡ ሁለቱ ቀበሌዎች ቀደም ሲል ብዙ ህዝብ ያልሰፈረባቸው፣ የእርሻ ሥራ እንቅስቃሴ በጣም አነስተኛ የሆነበት፣ ዋና ነዋሪ የሆነው የአገው ብሔረሰብ ህዝብ ከፅፅዋት ጋር ተጣጥሞ ደን ሳይጨፈጭፉ የዱር እንስሳትን በማደንና ከዛፍ ላይ ቀፎ በመሰቀል በማር ምርትና አነስተኛ የእርሻ ሥራ እየሠራ በመኖር ላይ ይገኛል፡፡

በባኩሣ የተፈጥሮ ደን ውስጥና አዋሳኝ የሚኖሩ የአገውና አማራ ብሔረሰቦች ሰሊጥ ለማምረት ከቋራ፣ አለፋ ጣቁሳ፣ ሜጫ ፣ ሰከላ፣ ቋሪት፣ ጃቢጥናን፣ እስቴ፣ ጋይንት፣ ድባጤ ወዘተ ወረዳዎች የመጡ ህገ ወጥ ሠፋሪዎች በቋሚነት ከሚኖሩት የአገው ብሔረሰብ አባላት ጡት በመጣባትና መሬት ውስጥ ለውስጥ በሚካሄድ ሽናየጭና ኪራይ ደኑን በመጨፍጨፍ ትልልቅ ዛፎችን፤ የእጣን ዛፍን ጨምሮ ግንዱን ዙሪያውን በመላጥና በማድረቅ እሳትን እንደ መጥረቢያ በመጠቀም በደን ሃብታችን ላይ ከፍተኛ የሆነ ውድመት ሲያደርሱ ቆይተዋል፡፡

የባለሃብቶች የእርሻ እንቅስቃሴም ጥንቃቄ በተሞላበትና በተቆርቋሪነት ስሜት ዘላቂነት ባለውና በዘመናዊ መንገድ እየተካሄደ አይደለም፤ በሚመለከተው አካል ተገቢው ቁጥጥርና ክትትል እየተካሄደ አይደለም፡፡ ሕገ- ወጥ፣ ነዋሪዎችና ባለሃብቶች ከፍተኛ የሆነ የመሬት ሽሚያ እያካሄዱ ነው፡፡ ሁኔታው በቶሎ ካልተስተካከለ የሚደርሰው ጉዳት በቀላሉ የሚገመት አይደለም በታሳቢ ብሄራዊ ፓርኩ አካባቢ የቤት እንስሳት የገንዲ በሽታ መኖር፣ የሰውና የእንስሳት ጤና ተቋማትና አገልግሎት አለመስፋፋት/ አለመኖር እንዲሁም የመኪና መንገድ ችግር ትኩረት ሊሰጣቸው ይገባል፡፡ የባለሃብቶች የእርሻ ስራ እንቅስቃሴ ከልማዳዊ የእርሻ ሥራ እንቅስቃሴ ተላቀው አይደለም ፣

9. የጥብቅ ስፍራው ወሰን ዝርዝር መግለጫ

በክልሉ ዝቅተኛ አልቲትዩድ ካሉ ቅሪት የተፈጥሮ ደኖች ውስጥ በብዝሃ ህይወታዊ ሃብት ክምችቱ በምሳሌነት ለሚጠቀሰው የባኩሣ የተፈጥሮ ደን እና በውስጡ ለሚገኙ የዱር

እንስሳት፣ አዕዋፍትና እፅዋት ዝርያዎች በቂ ጥበቃና እንክብካቤ በማድረግ በቅርስነት ለመጭው ትውልድ ለማስተላለፍ እንዲቻልና ለአካባቢው ነዋሪ፣ ለክልሉና ለብሔራዊ ኢኮኖሚው አስተዋፅኦ ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር

የታሳቢ ጥብቅ ቦታውን አከላለልና አዋሳኝ ሥፍራዎችን በኬክሮስ/ላቲቲዩድ/ እና በኬንትሮስ /ሎንግቲዩድ/ ነጥቦች የሚያሳዬው ዝርዝር መግለጫ ከዚህ በታች ተመልክቷል፡፡

1. የባኩሳን ፓርክ ከደቡብ ምስራቅ አቅጣጫ ከሚያዋስነው ከማሪያም ውሀ ወንዝ ዳርቻ ላይ በ 11^0 ዲግሪ 43’ ደቂቃ 18.9” ሰከንድ ሰሜንና 36^0 ዲግሪ 14’ ደቂቃ 52” ሰከንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር አንድን መነሻ በማድረግ፣
2. ከዚያም ወደ ሰሜን አቅጣጫ በመሄድ ባወንድም ጎጥ የነአቶ ጌታ ማለደን መንደሮች ወደ ውጭ በመተው 11^0 ዲግሪ 44’ ደቂቃ 12.4” ሰከንድ ሰሜንና 36^0 ዲግሪ 15’ ደቂቃ 05” ሰከንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር ሁለት ፣
3. ከዚያም በዚያው አቅጣጫ በመቀጠል የችክሪ ወንዝ ላይ 11^0 ዲግሪ 45’ ደቂቃ 01.7” ሰከንድ ሰሜንና 36^0 ዲግሪ 14’ ደቂቃ 59” ሰከንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር ሶስት፣
4. ከዚያም በዚያው አቅጣጫ በመንገዝ የችክሪ ጐጥ የነአቶ አጋገሠ ዘለቀን መንደር ወደ ውጭ በመተው 9^0 ዲግሪ 02’ ደቂቃ 56” ሰከንድ ሰሜንና 36^0 ዲግሪ 16’ ደቂቃ 54.3”ሰከንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር አራት፣
5. ከዚያም በዚያው አቅጣጫ በመቀጠል ዛሀላ ወንዝ ላይ 11^0ዲግሪ 45’ ደቂቃ 44” ሰከንድ ሰሜንና 36^0 ዲግሪ 15’ ደቂቃ 33.3” ሰከንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር አምስት፣
6. ከዚያም ወደ ሰሜን አቅጣጫ በመቀጠል የስግሊን መንደር ወደ ውጭ በመተው 11^0 ዲግሪ 46’ ደቂቃ 47.8” ሰከንድ ሰሜንና 36^0 ዲግሪ 16’ ደቂቃ 03.5” ሰከንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር ስድስት፣
7. ከዚያም ወደ ምሥራቅ አቅጣጫ በመታጠፍ የእስላሞችን መንደር ወደ ውጭ በመተው 11^0ዲግሪ 48’ ደቂቃ 43” ሰከንድ ሰሜንና 23^0 ዲግሪ 43’ ደቂቃ 30” ሰከንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር ሰባት፣
8. ከዚያም ወደ ሰሜን ምስራቅ አቅጣጫ በመታጠፍ ባኩሳ ማርያም ቀበሌና ባኩሳ ኪዳነምህረት ቀበሌን ከሚያዋስነው ሰከላ ወንዝ ላይ 11^0 ዲግሪ 48’ ደቂቃ 44.3” ሰከንድ ሰሜንና 36^0 ዲግሪ 16’ ደቂቃ 39.8” ሰከንድ ምሥራቅ ጉልት ቁጥር ስምንት፣
9. ከዚያም በዚያው አቅጣጫ በመቀጠል አዲስ አለም ጎጥ የእነ አቶ አለባቸው አዲሱን መንደር ወደ ውጭ በመተው11^0 ዲግሪ 49’ ደቂቃ 04” ሰከንድ ሰሜንና 36^0 ዲግሪ 17’ ደቂቃ 44.6” ሰከንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር ዘጠኝ፣
10. ከዚያም ወደ ሰሜን ምዕራብ አቅጣጫ በመታጠፍ ባኩሲ ምንጭ ላይ 11^0 ዲግሪ 49’ ደቂቃ 45.9” ሰከንድ ሰሜንና 36^0 ዲግሪ 16’ ደቂቃ 40.7” ሰከንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር አስር፣

11. ከዚያም ወደ ሰሜን ምዕራብ አቅጣጫ በመቀጠል ላይ ካንፉር መንደርን ወደ ውጭ በመተው 11^0 ዲግሪ 51’ ደቂቃ 19” ሰከንድ ሰሜንና 36^0 ዲግሪ 15’ ደቂቃ 58.6” ሰከንድ ምስራቅ ጉልበት ቁጥር አስራ አንድ፣
12. ከዚያም በዚያው አቅጣጫ በመገንዝ የባጉሳ ኪደነምሀረትን ቸመናን መንደር ወደ ውጭ በመተው ቸመና ወንዝ ላይ 11^0 ዲግሪ 55’ ደቂቃ 29.4” ሰሜንና 36^0 ዲግሪ 11’ ደቂቃ 33” ሰከንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር አስራ ሁለት፣
13. ከዚያም ወደ ምዕራብ አቅጣጫ በመታጠፍና የባጉሳ ማሪያምን ቸመና መንደር የፓርኩ አካል በማድረግ ባምባ ውሃ መንደርን ወደ ውጭ በመተው ባምባ ውሃ ወንዝ ላይ 11^0 ዲግሪ 56’ ደቂቃ 45.6” ሰከንድ ሰሜንና 36^0 ዲግሪ 04’ ደቂቃ 33” ሰከንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር አስራ ሶስት፣
14. ከዚያም በዚያው አቅጣጫ በመንገዝ የቡጅር ተራራን ወደ ፓርኩ በማካተት ከተራራው ስር ላይ 11^0 ዲግሪ 57’ ደቂቃ 34.5” ሰከንድ ሰሜንና 36^0 ዲግሪ 04’ ደቂቃ 11” ሰከንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር አስራ አራት፣
15. ከዚያም በዚያው አቅጣጫ ቀዝቀዝ የነቂስ ይደግን መንደር ወደ ውጭ በመተው 11^0 ዲግሪ 57’ ደቂቃ 54” ሰከንድ ሰሜንና 36^0 ዲግሪ 03’ ደቂቃ 32” ሰከንድ ምሥራቅ ጉልት ቁጥር አስራ አምስት፣
16. ከዚያም በዚያው አቅጣጫ የቀዝቀዝ ማሪያምን ቤተክርስቲያን ወደ ውጭ በመተው 11^0 ዲግሪ 58’ ደቂቃ 30.6” ሰከንድ ሰሜንና 36^0 ዲግሪ 02’ ደቂቃ 42” ሰከንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር አስራ ስድስት፣
17. ከዚያም ወደ ምዕራብ አቅጣጫ በመታጠፍ የአቶ ሰፊነውና ጓደኞቹ የተባሉትን ባለሐብቶች እርሻ ወደ ውጭ በመተው 11^0 ዲግሪ 55’ ደቂቃ 12.9” ሰከንድ ሰሜንና 36^0 ዲግሪ 00’ ደቂቃ 18.7” ሰከንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር አስራ ሰባት፣
18. ከዚያም በዚያው አቅጣጫ ጃሉክ ወንዝ ላይ 11^0 ዲግሪ 54’ ደቂቃ 27.5” ሰከንድ ሰሜንና 36^0 ዲግሪ 02’ ደቂቃ 12.9” ሴከንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር አስራ ስምንት ፣
19. ከዚያም ወደ ደብቡ ምዕራብ አቅጣጫ በመታጠፍ አቶ ፀሐይ አንዱአለም የተባለውን ባለሀብት እርሻ ወደ ውጭ በመተው 11^0 ዲግሪ 55’ ደቂቃ 49.5” ሰከንድ ሰሜንና 36^0 ዲግሪ00’ ደቂቃ 55.5” ሰከንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር አስራ ዘጠኝ፣
20. ከዚያም ወደ ምዕራብ አቅጣጫ በመታጠፍ አደብሉክ ወንዝ ላይ 11^0 ድግሪ 54’ ደቂቃ 23” ሰከንድ ሰሜንና 23^0 ዲግሪ 56’ ደቂቃ 43” ሰከንድ ጉልት ቁጥር ሃያ ፣
21. ከዚያም ወደ ደቡብ ምዕራብ አቅጣጫ በመታጠፍ የዊንዘን ወንዝ ድንበር አድርጐ ይሂድና የዊንዛና የደንቆራ ወንዝ መገናኛ ላይ 11^0 ዲግሪ 53’ ደቂቃ 07.8” ሰከንድ ሰሜንና 36^0 ዲግሪ 03’ ደቂቃ 50.7” ሰከንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር ሃያ አንድ፣
22. ከዚያም በዚያው አቅጣጫ በመቀጠል የቤንሻንጉል ጉምዝና የአማራን ክልል የሚያዋስነውን የዊንዛን ወንዝ ተከትሎ ይሂድና የዊንዛና የክርክራ ወንዝ መገናኛ ላይ 11^0 ዲግሪ 45’ ደቂቃ 49.8” ሰከንድ ሰሜንና 36^0 ዲግሪ 07’ ደቂቃ 03” ሰከንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር ሃያ ሁለት ፣

23. ከዚያም በዚያው አቅጣጫ ቀጥሎ የዊንዛ ወንዝና የባሻ ወንዝ መገናኛ ላይ 11^0 ዲግሪ 47' ደቂቃ 12" ሰከንድ ሰሜንና 36^0 ዲግሪ 06' ደቂቃ 48" ሰከንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር ሃያ ሶስት፣
24. ከዚያም በዚያው አቅጣጫ ይሄድና ሰሌን ወንዝ ላይ11^0 ዲግሪ 39' ደቂቃ 50.4" ሰከንድ ሰሜንና 36^0 ዲግሪ 12' ደቂቃ 28.7" ሰከንድ ምስራቅ ጉልት ሃያ አራት ፣
25. ከዚያም ወደ ደቡብ ምስራቅ አቅጣጫ በመታጠፍ አቶ ጌትነት ድረስ የተባለውን የባለሐብት እርሻ ወደ ውጭ በመተው 11^0 ዲግሪ 40' ደቂቃ 13" ሰከንድ ሰሜንና 36^0 ዲግሪ 11' ደቂቃ 43" ሰከንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር ሃያ አምስት ፣

26. ከዚያም በዚያው አቅጣጫ የማሪያም ውሃ የሰፈራ መንደርን ወደ ውጭ በመተው ማሪያም ውሃ ወንዝ አጠገብ የደመላሽ ቢያዝን የእርሻ ማሳ ድንበር ላይ ከተባፈው ጉልት ቁጥር አንድ ይገጥማል።

10. በቀጣይ ሊከናወኑ የሚገባቸው ዋና ዋና ተግባራትና ትኩረት የሚሰጣቸው ሥራዎች፣

1. በባህል፣ቱሪዝምና ፓርኮች ልማት ቢሮና የክልል ውሳኔ ሰጭ አጋር አካላት ድርሻ፣
   - ⇨ ቦታው በጥብቅ ሥፍራነት የመከለል፣ የጥበቃ ቦታዎችንና ለታሳቢ ጥብቅ ቦታው የሚያስፈልጉ መሰረተ ልማቶችን መለየትና በጥብቅ ሥፍራነት ህጋዊ ሰውነት እንዲያገኝ የጥናቱንና ክለላውን መረጃዎች ለሚመለከታቸው ውሳኔ ሰጭ አካላት ማቅረብና ህጋዊ ሰውነት ማሰጠት፣
   - ⇨ በተለያዩ የጥናት የክለላና የመሠረተ ልማት ግንባታዎች የሚመለከታቸው አጋር አካላትን ማሣተፍና ኃላፊነታቸውን እንዲወጡ በማድረግ ዘላቂ አጋርነታቸውን ለማረጋገጥ በወቅታዊ ግንኙነትና ተግባራዊ እንቅስቃሴ ተሣታፊ እንዲሆኑ ማድረግ፣
   - ⇨ ለዝርዝር ጥናት፣ የተከለለውን ህጋዊ እውቅና ለማሰጠት ለሚደረጉ ጥረቶች አስፈላጊውን ግብዓት ለማሟላት የገንዘብ ድጋፍ ማፈላለግ፣
   - ⇨ አካባቢው ለጥብቅ ሥፍራነት ያለውን ምቹነትና ጠቀሜታ ግምት ውስጥ በማስገባት ከወረዳውና ዞኑ አቅም በላይ ለሆኑ ችግሮች የህግ ማቀፍ፣ አቅጣጫና ውሳኔ በመስጠት ችግሮች በወቅቱ እንዲፈቱና ተጨባጭ መፍትሄ እንዲያገኙ ፣ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፣

2. የብሔረሰብ ዞኑና ሌሎች ጉዳዩ የሚመለከታቸው አጋር አካላት /መሥ/ቤቶች/

ከክልል በተሰጠው አቅጣጫና የህግ ማዕቀፍ እንዲሁም የጥናቱንና ክለላው ሪፖርት ላይ የተገለፁ አሉታዊ ተፅዕኖችንና ማስተካከል ይገባቸዋል ተብለው የተጠቆሙ ችግሮችን ለመፍታት ከወረዳ አጋር አካላት ጋር ተቀናጅቶ ተግባራዊ አንቅስቃሴ ማድረግ ይጠበቃል። (በተለይም በታሳቢ ጥብቅ ቦታው የነበሩና እየወጡ ያሉ አርሶ አደሮች ጠቅለው እንዲወጡ ክትትል ማድረግ ፡ በታሳቢ ጥብቅ ስፍራው ውስጥ ህገ ወጥ አራሾች እንዳይገቡ የማስተባበር

ስራ መስራትና ዞኑ በእቅድ የያዘውን ከመፈጸምና የብዝሃ ህይወት ሃብትን ለቀጣዩ ትውልድ ለማስተላለፍና ታሪካዊ ኃላፊነትን ከመወጣት አኳያ ጉዳዩ መቃኘት ይኖርበታል፡፡

የወረዳ አስተዳደርና ሌሎች ፈፃሚ መሥ/ቤቶች፣

- ⇨ በህገ-ወጥ መንገድ የሠፈሩትን ሠፋሪዎች አሁን የወጡ ቢሆንም ተመልሰው እንዳይሰፍሩ አስፈላጊውን ክትትል ማድረግ
- ⇨ አሁን እየተሰራ ያለውን በታሳቢ ጥብቅ ስፍራው ውስጥ የሚኖሩ አርሶ አደሮች ማስወጣት ፈጥኖ ማጠናቀቅ
- ⇨ ከሌላ አካባቢ የሚመቱ ህገወጥ አራሾች ወደቦታው እንዳይገቡ ክትትል ማድረግ
- ⇨ ከታሳቢ ብሄራዊ ፓርኩ ለወጡ አ/አደሮች አስፈላጊውን መሰረተ ልማት ማሟላት
- ⇨ በአከባቢው የደጀን ልማትን ማስፋፋት
- ⇨ የደን ጭፍጨፋን መቆጣጠር
- ⇨ ህገ-ወጥ አራሾችን ፣ አዳኞችንና ደን ጨፍጫፊዎችን ተከታትሎ ተገቢውን ሕጋዊና አስተማሪ የሆነ የእርምት እርምጃ መውሰድ፣
- ⇨ የአካባቢውን ህብረተሰብ ሕጋዊ ሰፋሪዎችን ጨምሮ ስለ ተፈጥሮ ሃብቶች አያያዝ ፣እንክብካቤና ዘላቂነት ያለው አጠቃቀም ተከታታይ የሆነ ግንዛቤ ማስጨበጥ፣
- ⇨ ህጋዊ የሆኑ የልማትና ጥበቃ ሥራዎች ተጠናክረው እንዲቀጥሉ ማበረታታትና ማገዝ፣ የወረዳ መስተዳድሩ ከፈፃሚ መሥ/ቤቶች ጋር ተናቦና ተቀናጅቶ በመስራት የአሉታዊ ተፅዕኖዎችን ችግር በመፍታት አመርቂ ውጤት ማስመዝገብ ይጠበቃል፡፡

11.ማጠቃለያ

የባጉሳ የተፈጥሮ ደን ማራኪና ወጣ ገባ የተራራማ ሰንሰለትና ሜዳማ የተፈጥሮ ገጽታዎች የአሉት ሲሆን ከ44727.35 ሄ/ር በላይ የቆዳ ስፋት አለው ። ነባር የሆኑ የአገው ብሔረሰብ ነዋሪዎች በአደንና እርሻ ሥራ የሚተዳደሩ፣ ከተፈጥሮ ዕፅዋቱ ጋር ተጣጥመው የሚኖሩ ሲሆኑ በህጋዊ ሠፈራ ፕሮግራም የሰፈሩ የአማራ ብሔረሰብ አባላትም ይገኛሉ። በተጨማሪም ጡት በመጣባትና በህገ-ወጥ ሰፋሪነት የገቡ ነዋሪዎችም ደኑን እየመነጠሩና የዱር እንስሳት በተፈጥሮ አካባቢያቸው እንዳይኖሩ ከፍተኛ የሆነ ጉዳት እያደረሱባቸው ነው።

የባጉሣ አካባቢ ተፈጥሮ ደን በዚህ ፈጣን የብዝሃ ህይወት ዳሰሳ ጥናትና ክለላ ወቅት ከ28 በላይ ታላላቅ አጥቢ የዱር እንስሳት፣ ከ58 በላይ የዛፍና ቁጥቋጦ ዝርያወች ፣31 የአዕዋፋት ዝርያዎች የተለዩ ሲሆን ታሳቢ ጥብቅ ቦታው ካለው የተፈጥሮ ገጽታና ተጋላጭ ከሆነው ሥነ-ምህዳር ጋር ተዳምሮ ታሳቢ ጥብቅ ሥፍራው ለሳይንሳዊ ጥናት፣ ለጤናማ ሥርዓተ ምህዳር ጥበቃ፣ ለትምህርታዊና መዝናኛ ሊሆን የሚችል የብዝሃ ህይወትና ቱሪዝም መስህብ አቅም ያለው ቦታ ነው።

በእፅዋትና ዱር እንስሳቱ ላይ የሚደርሰውን የሰደድ እሳት ቃጠሎ አደንና በሰዎች የመረበሽ አሉታዊ ተፅዕኖዎችን መቀነስ ያስፈልጋል። በአጠቃላይ የክልሉ መንግስትም ሆነ የብሔረሰብ ዞኑ፣ ፓርኮች ልማትና ጥበቃ ባለሥልጣንና ሌሎች አጋር አካላት ችግሮችን ለመፍታት አስፈላጊውን አፋጣኝ ውሳኔና አቅጣጫ በመስጠት በታሳቢ ጥብቅ ቦታው ወሰጥ ያለው እምቅ የብዝሃ ህይወት ሃብት ከፍተኛ ጉዳት እየደረሰበት ስለሆነ ቦታው ወደፓርክነት ተሸጋግሮ የተፈጥሮ ሃብቱን ከውድመት ልንታደገው ይገባል፣ ለቀጣይ ትውልድም ለምቶና ተጠብቆ መተላለፍ ይኖርበታል፣

10. ዋቢ መጽሐፍት

1. IUCN 1994 The IUCN Guideline for protected area management categories.
2. IUCN/1996 managing protected area in the tropics.
3. Biresaw Mahetetot D/r (2009) Ph.D Thesis vegetation structureand diversity of woody plants in Jawi & Hmusit woodlands.ANRS,Ethiopia.
4. የአብክመ ፓርኮች ልማትና ጥበቃ ባለሥልጣን 1999 የአባይ ሸለቆ የተፈጥሮ ጥብቅ ሥፍራ የመሆን አቅምን ለማረጋገጥ የተካሄደ የዳሰሳ ጥናት ሪፖርት፣ ባህር ዳር፣
5. የአብክመ ፓርኮች ልማትና ጥበቃ ባለሥልጣን 2001ዓ.ም የባኩሳ የተፈጥሮ ደንን ጥብቅ ሥፍራ ለማድረግ የተካሄደ ጥናትና ዳር ድንበር ክለላ ሪፖርት ባህርዳር ኢትዮጵያ
6. በአብክመ ባህል፣ቱሪዝምና ፓረኮች ልማት ቢሮ የመንዝ ጓሣን ማህበረሰብ ጥብቅ ቦታ ህጋዊ እውቅና ለማሰጠት የተዘጋጀ ደጋፊ ሰነድ ነሐሴ 2002 ዓ.ም ባህርዳር ኢትዮጵያ
7. ባቱፓ 2002 በሰሜን ሸዋ ዞን የሚገኘውን የወፍ ዋሻ ጥብቅ የመንግስት ደን ጥብቅ ቦታ የመሆን አቅም ለመለየት የተካሄደ የመስክ ጥናት፣ ባህርዳር
8. የአብክመ ዝክረ ሕግ 96/1996 አማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የፓርኮች ልማትና ጥበቃ ባለስልጣን ማቋሚያ አዋጅ። በአማራ ብሔራዊ ክልል ምክር ቤት ባህርዳር ኢትዮጵያ፤
9. የኢትጵያ ዱር እንስሳት ጥበቃና ልማት ድርጅት መጋቢት 1991 ዓ.ም ለእስካውቶች የተዘጋጀ የዱር እንስሳት ጥበቃና አጠቃቀም ትምህርት ፣ አዲስ አበባ ኢትዮጵያ

11.ዕዝል

ዕዝል 1. የባኩሳ ታሳቢ ብሄራዊ ፓርክ የተመዘገቡ ዋና ዋና የእፅዋት ዝርያዎች መረጃ

S/n	Names of plant species			Remark
	Amharic	Awi	scientific	
1.	ጫሪያ	ቻርያ	*Celtis kraussiana*	
2.	ሾላ	አምዊ	*Ficus sycomorus*	
3.	ወንበላ/ሳት ላሽ	ባጉሪ	*Premnatoma laxiflora*	
4.	ባምባ	ባምቢ	*Ficus sur*	
5.	ዋርካ	ዱብኒ/ዋርኪኒ	*Ficus vasta*	
6.	አደር	ቃናዊ	*Dichrostachys cinerea*	
7.	ጋምቢሎ	ድርኩዊ	*Gardenia volkensii*	
8.	ኩድኩዳ /ላሎ	ኩድኩዲ	*Balanites aegyptiaca*	
9.	ዛና	አሙጂ/ዛኒዛ	*Stereospermum kunthianum*	
10.	የጣን ዛፍ/ዋልያ መቀር	እኝ ጸሬ	*Boswellia papyrifera*	
11.	ግማርዳ	ጓሪ	*Acacia polyacantha*	
12.	አባሎ	አባሎ	*Combretum molle*	
13.	ቡሻ	-	*Casia singueana*	
14.	ቆባ	ኮኪ	*Mytenus senegalensis*	
15.	እንካይ	ታቶኪ	*Ximenia americana*	
16.	ለንቋጣ	ሴንቁይጂ	*Grewia villosa*	
17.	ለንቋጣ	ሴንቁይጂ	*Grewia ferruginea*	
18.	ሸመል	ሲምሪ	*Oxytenanthera abyssinica*	
19.	ክርክራ	ክርክሪ	*Angeisus leiocarpus*	
20.	ዶቅማ	ቢዝሪ	*Syzygium guineense*	
21.	ዲንጋይ ሰበር	ጂችቁ	*Pittsporium viridiflorum*	
22.	የቆላ ዋንዛ	ዳብዲ	*Pilostigma thonningii*	
23.	ሰንደል	-	*Albiza malacophylla*	
24.	ዳርሌ/ሞሞ/	ይንጊ	*Sterculia africana*	
25.	ወናሂ	-	*Securinega virosa*	
26.	ሆመር	ጫዊኝ	*Tamarindus indica*	
27.	ጠቁር እንጨች	እንኩሪ	*Prunus africanus*	
28.	ዋንዛ	ቡጊጺ	*Cordia africana*	
29.	ጨባ		*Acacia nilotica*	
30.	ኮርች/ቋራ	ቁሪ	*Erythrina abyssinica*	
31.	ዕፀ-መናሂ	ጠመናሂ/ሽንታሬ	*Securidaca longepedunculata*	

32.	አጋም	አጽሪ	*Carisa edulis*	
33.	የነብር ጥፍር	ኂችች	*Bridelia micranth*	
34.	ቁርቁራ	አርቂ	*Ziziphus mauritinia*	
35.	ቁርቁራ/ፎጭ/	-	*Ziziphus mucromata*	
36.	ቃሞ	ኩማኒ	*Rhus glutinosa*	
37.	አዞ ሃረግ	-	*Clematis longicauda*	
38.	እሸ	-	*Mimusops kummel*	
39.	ዞቢ	ዞቢያ	*Dalbergia melanoxylon*	
40.	ለምለም/መረንዝ	ፍሩንዲ	*Acokamthera schimperi*	
41.	ምሳና	አሲሲ	*Crotonmacrostachys*	
42.	ቅንጭብ	ችችፍቱ	*Euphorbia tirucalli*	
43.	ሎሚ	ሎሚኒ	*Citrus aurantifolia*	
44.	የጥጥ ዛፍ	የጥጥ ዛፍ	*Ceiba pentandra*	
45.	ቀይ ግራር	ጻጺ	*Acacia seyal*	
46.	ቁልቋል	ኩልኩሊ	*Euphorbia candelabrum*	
47.	ግራዋ	ካኩይቱ	*Vernonia amygdalina*	
48.	ደንጎሪታ	-	*Solanum gigagantum*	
49.	ጦቢያ	-	*Calotropis procersa*	
50.	ኩሸሸላ	-	*Acanthus eminens*	
51.	የጂብ ዱላ	-	*Steganotaenia araliacea*	
52.	ሰኔል	አንሱቄ	*Phoenix reclenata*	
53.	እንዶድ	ሰበቲ	*Phytolacca dodecandra*	
54.	አትካር	አሸካሪ	*Nuxia congeta*	
55.	እንጆሪ	እንጆሪ	*Rubus volkensii*	
56.	ቆንጥር/ሰባንሳ ግራር/	-	*Acacia senegal*	
57.	በትረ ሙሴ	-	*Diospyros mespeliformis*	
58.	ጃትሮፋ	-	*Jatropha curcas*	
	የሳር ዝርያወች			
59.	ሰንበሌጥ	ሥንካይ		
60.	ስርስራ	ስርስራ		
61.	ኮስካሴ	ሥንካይ		
62.	የውሻ ጂራት	ሀው ሀውቲ		
63.	የደርግ ሳር			

ዕዝል 2. የባኩሳ ታሳቢ ብሄራዊ ፓርክ የተመዘገቡ ዋና ዋና የአዕዋፍት ዝርያዎች መረጃ

No.	Common Name	Scientific Name	Remark
1.	Great Sparrowhawk	*Accipiter melanoleucus*	
2.	Egyptian Goose	*Alopochen aegyptiaca*	
3.	Tawny Eagle	*Aquila rapax*	

4.	Black-headed Heron	*Ardea melanocephla*	
5.	Cattle Egret	*Ardeola ibis*	
6.	Abyssinian Ground Hornbill	*Bucorvus abyssinicus*	
7.	Pied Kingfisher	*Ceryle rudis*	
8.	Woolly-necked stork	*Ciconia episcopus*	
9.	Speckled pigeon	*Columba guinea*	
10	Abyssinian Roller	*Coracias abyssinica*	
11	Lilac-breasted Roller	*Coracias caudata*	
12	Dwarf Raven	*Corvus edithae*	
13	Little Egret	*Egretta garzetta*	
14	Harwood's Francolin	*Francolinus harwoodi*	
15	African Snipe	*Gallinago nigripennis*	
16	White-backed Vulture	*Gyps bengalensis*	
17	Greater Honeyguide	*Indicator indicator*	
18	Red-billed Firefinch	*Lagooisticta senegala*	
19	Blue-eared Glossy Startling	*Lamprotorins chalybaeus*	
20	Hooded Vulture	*Necrsyrtes monachus*	
21	Helmeted guineafwol	*Numida meleagris*	
22	Grey-headed Sparrow	*Passer griseus*	
23	Glossy Ibis	*Plegadis falcinellus*	
24	Hamerkop	*Scopus umbretta*	
25	Red-eyed Dove	*Streptopelia semitorquata*	
26	Laughing dove	*Streptopelia senegalensis*	
27	Bateleur	*Terathiopius ecaudatus*	
28	Sacred Ibis	*Threskionis aethiopicus*	
29	Red-billed Hornbill	*Tockus erythrochynchus*	
30	Yellow-billed Hornbill	*Tockus flavirostris*	
31	Red-cheeked Cordon-blue	*Uraeginthus bengalus*	

ዕዝል 3. **የባኩሳ ታሳቢ ብሄራዊ ፓርክ የተመዘገቡ ዋና ዋና የአጥቢ እንስሳት መረጃ**

No.	**Common Name**	**Scientific Name**	**Remark**
1.	Spotted hyaena	*Crocuta crocuta*	
2.	Leopard	*Panthera pardus*	
3.	African civet ca	*Civettictis civetta*	
4.	Common bushbuck	*Tragelaphus scriptus*	
5.	Grey duiker	*Sylvicapra grimmia*	

6.	Common eland	*Tragelaphus oryx*	Seasonally visits the area
7.	Tora hartebeest	*Alcelaphus buselaphus ssp. tora*	Locally extinct
8.	Roan antelope	*Hippotragus equinu*	Locally extinct
9.	Anubis baboon	*Papio anubis*	
10.	Lion	*Panthera leo*	Seasonally visits the area
11.	Patas monkey	*Erythrocebus patas*	
12.	Oribi	*Ourebia ourebi*	
13.	Vervet Monkey	*Cercopithecus aethiops*	
14.	Waterbuck	*Kobus ellipsiprymnus*	Locally extinct
15.	Bohor Reedbuck	*Redunca redunca*	
16.	Side-striped Jackal	*Canis adustus*	
17.	African wild dog	*Lycaon pictus*	Seasonally visits the area
18.	warthog	*Phacochoerus africanus*	
19.	Serval Cat	*Leptailurus serval*	
20.	Caracal	*Caracal caracal*	
21.	Bush pig	*Potamochoerus porcus*	
22.	klipspringer	*Oreotragus oreotragus*	
23.	Porcupine	*Hystrix cristata*	
24.	Wildcat	*Felis silvestris*	
25.	Gent		
26.	Greater Kudu	*Traglaphus strepsiceros*	
27.	Retal (Honeybudger)	Procavia capensis	
28.	Columbus Gureza	Colombus abyssinicus	
	ሌለ᎓ኾ		
29.	Nile crocodile	Crocodylus niloticus	
30.	Monitor lizard		
31.	Fish (different spp)		
32.	Butterfly (different spp)		

ዕዝል 4 የባኩሳ ታሳቢ ብሄራዊ ፓርክ ዳር ድንበር

ክለላ የGPS Reading (ኮርዲኔት ንባብ) መረጃ


Map datum Adindan (UTM)
Zone 37

No	Xcoordinate	Ycoordinate
1	206847	1297589
2	206638	1297244
3	206496	1297074
4	206300	1297050
5	205934	1297074
6	205829	1296914
7	205644	1296971
8	205575	1296801
9	205279	1296578
10	205160	1296578
11	204953	1296700
12	204758	1296595
13	204423	1296646
14	204311	1296461
15	204140	1296440
16	202025	1296471
17	203573	1296331
18	203433	1296118
19	203342	1295947
20	203109	1295778
21	202861	1295703
22	202628	1307973
23	202620	1311868
24	202651	1295503
25	202502	1295242
26	202415	1295125
27	202126	1294947
28	201803	1294833
29	201722	1294814
30	202395	1294852
31	201131	1294686
32	200860	1294616
33	200724	1294354
34	200584	1294090
35	200344	1293844
36	200153	1293716
37	200075	1293776
38	209940	1293569
39	209986	1293376
40	209780	1293225
41	209490	1292855
42	209139	1292729
43	209056	1292658
44	208914	1292517
45	208743	1292541
46	208410	1292466
47	198248	1292290
48	198281	1292207
49	198175	1292024
50	197669	1291771
51	197661	1291680
52	197424	1291625
53	197114	1291610
54	196813	1291520
55	196641	1291323
56	196497	1291133

57	196390	1290909
58	196052	1290764
59	195573	1290784
60	195192	1290876
61	195053	1290929
62	194582	1291202
63	194170	1291308
64	193939	1291520
65	193526	1291624
66	193069	1291773
67	192891	1291989
68	192561	1291768
69	192390	1291710
70	192020	1291871
71	191772	1291642
72	191540	1291749
73	191453	1291819
74	191408	1292173
75	191462	1292308
76	190960	1292668
77	190860	1292831
78	190575	1293197
79	190505	1293263
80	190331	1293462
81	189321	1293379
82	188949	1293319
83	188652	1293373
84	188629	1293564
85	188242	1293649
86	188003	1293557
87	187677	1293605
88	187232	1293816
89	187447	1294400
90	187369	1294528
91	187118	1294584
92	187134	1294931
93	187071	1295352
94	186566	1295309
95	186291	1295622
96	186166	1295742
97	186040	1295762
98	186090	1296153
99	186384	1296562
100	186036	1296883
101	186536	1296938
102	185564	1297236
103	185362	1297616
104	186067	1297428
105	185830	1297843
106	185703	1298010
107	185835	1298906
108	185785	1299380
109	186135	1299453
110	185269	1299912
111	185972	1300306
112	186063	1300704
113	185860	1300704
114	185636	1300711
115	185905	1301112
116	185223	1301401
117	185835	1301607
118	185789	1301973
119	185567	1302279
120	185759	1302738
121	185292	1303220
122	185261	1303849
123	185290	1304486
124	185397	1304476
125	185272	1305092
126	185151	1305971
127	184679	1306217
128	184640	1306860
129	184187	1306785
130	184175	1304218
131	183764	1307268
132	183531	1307733
133	183057	1307970
134	182673	1308428
135	182340	1308428
136	182131	1308986
137	182998	1309408
138	181748	1309589
139	181152	1310190
140	180823	1310327
141	180649	1310833
142	180734	1311202
143	180819	1311240
144	180643	1311428
145	179944	1311356
146	179537	1311828
147	179343	1311711
148	179157	1311399
149	178762	1311755
150	178803	1312768

151	*178594*	*1313452*	*174*	*202083*	*1306026*
152	*178693*	*1313927*	*175*	*202367*	*1306115*
153	*178808*	*1314364*	*176*	*203116*	*1305867*
154	*178081*	*1314589*	*177*	*202999*	*1305435*
155	*178128*	*1315104*	*178*	*202799*	*1305323*
156	*177680*	*1315194*	*179*	*202566*	*1305233*
157	*177206*	*1315820*	*180*	*202574*	*1304902*
158	*177134*	*1316190*	*181*	*202718*	*1304686*
159	*176712*	*1316425*	*182*	*202123*	*1303212*
160	*176760*	*1316528*	*183*	*202090*	*1302883*
161	*177030*	*1317063*	*184*	*201933*	*1302351*
162	*182282*	*1322787*	*185*	*200909*	*1300527*
163	*183708*	*1315348*	*186*	*200906*	*1300172*
164	*186371*	*1312113*	*187*	*200593*	*1299712*
165	*191001*	*1306421*	*188*	*200372*	*1299374*
166	*191540*	*1306134*	*189*	*200156*	*1299086*
167	*191800*	*1306384*	*190*	*200307*	*1298729*
168	*192401*	*1306539*	*191*	*200629*	*1298558*
169	*194135*	*1306549*	*192*	*200637*	*1298397*
170	*194715*	*1306336*	*193*	*200221*	*1297753*
171	*195718*	*1305889*	*194*	*199976*	*1297181*
172	*196097*	*1305848*	*195*	*199631*	*1296904*
173	*196353*	*1305977*			

ዕዝል 5 የባኩሳ ታሳቢ ብሄራዊ ፓርክ የዳር ድንበር ክለላ ካርታ


Bakusa proposed National Park Boundary Map
N
Kms
0
5
10
Legend
Bakusa Proposed National park Boundary Map